

# አራጣ!

**የጐንቻው !**




በአስራ አንድ ስሌት ምናብ በሚያውር፤
ሃያ አመት በብድር 'ያረገች' አገር፤
እንዲህ ጠድፋ ከንፍስ ስትሽከረከር፤
ከአፍሪቃ እንዳትወጣ እንዳትለቅ ምህዋር፤
መያዣም አስያዦች እንዳንወድቅ ጠፈር፤
በትብታችን አምላክ ችንካር እንወድር፤
ባዕዳን እንዳይጦልቧት እንዳትሰወር፤
አንጡራ ሃብታችን ከከርሷ እንዲኖር፤
'ዜሮ እንዳንባዛ' 'በዞረ ድምር'፤
የአራጣ ባላንጣ አያቀምስ አፈር፤
ዝግ የሸረበብን አርጎን ባይታወር፤
ደበኛ ፓርላማ ትውልድ ባገሩ እማያቃብር፤
እዳን ለባለዕዳው ሕዝቡም ባላገር፤
**ወያኔ አራጣውን ወለዱን ይቁጠር።**

በዕዳ ተከናንባ በችግር ተዘፍቃ፤
ተገፋ፤ ተዘርፋ ለጥሪት ሳትበቃ፤
ከፍላ ተከፋፍላ ዓይነቷን ተነጥቃ፤
ጸጋዋ ተገፎ እርቃኗን ወዳድቃ፤
ክብሯ ስሟ ጎድፎ በልመና ታውቃ፤
ሕዝቧ ጦሙን ሲያድር ለባዕድ ሰንቃ፤
አራጣ ተጭኗት ሃያ ዓመት ደቃቃ፤
አገሬ ተሳስራ በባንዳዎች ታንቃ፤
አደገች ይሏታል መጠቀች ጨረቃ፤
**ደልለው 'ሊያቀኗት' በቁጥር 'እቃ፤እቃ'።**

ቻይና እና አሜሪካ እያቆላመጡ፤እየቀላወጡ፤
በአራጣ 'ሊገዟት' ባዕዶች የቋመጡ፤
ሊበሏት ያሏትን 'ክሽን' ስም ሲያወጡ፤
'ፉርሽካ' አደልበው ብልት ሊቃረጡ፤
ዓሳ – ነባሪዎች አገር የሚውጡ፤
ያንሱ አራጣቸውን ዓይነት እንዳያጡ፤
ሃራጅ የሸጠንን ወያኔን ይጋጡ፤
ሕዝብ አገር አክስረው በትርፍ የናጠጡ፤
የቱጃር ደላሎች 'በመስቀል ይቀጡ'፤
ሂሳብ እንድንዘጋ በውሉ በቅጡ፤
ሃያ ዓምት እዳዎች ወያኔዎች 'ይንጡ'፤
**'እንድንገላገል' 'ወለድ-ያረገዙት' 'ቀነኞች' ያምጡ።**

***ማስታወሻ፡-*** *ሰሞኑን በዝግ ፓርላማ ተኮልኩለው ሲያልቧትም፤ሲበሏትም የኖረችውን መንታላ ሀገራችንን ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን በዓለም ገበያ አስይዘው የአራጣ ብድር ይዘርፉ ዘንድ ያሴሩብንን ወያኔዎችና ግብረ በሎችን ቆርጠን እንድንዋጋቸው ማሳሰቢያ ትሁን ዘንድ እነሆ።*

*የጐንቻው! 14.11.14*